## 5S ፋውንዴሽን

5S ፕሮጀክት በብራይተን እና በሰሴክስ ሜዲካል ትምህርት ቤት (BSMS) በአለም አቀፍ ጤና እና ኢንፌክሽኖች ትምህርት ክፍል (GHI) ከምስራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ የማህበራዊ ሳይንስ ምርምር ድርጅት (OSSREA) ጋር በመተባበር እየተተገበረ የሚገኝ የምርምር ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት በሚገኙ ሁለት ዓይነት የቆዳ በሽታዎች ማለትም ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ ወይም የእግር እብጠት እና እከክ ላይ ትኩረት በማድረግ ይሠራል።


**ፕሮፌሰር ጌትነት ታደለ (ፕሮጀክት መሪ)**

getnett2001@yahoo.com

www.ossrea.net

+251111239484

5S Foundation Ethiopia



FUNDED BY NIHR | National Institute for Health Research

UKaid from the British people




# ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ

## (የእግር እብጠት)

ይህ መልዕክት በጤና ሚኒስቴር ትኩረት የሚሹ የሃሩራማ አካባቢዎች በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከተዘጋጀ አጭር መመሪያ የተወሰደ ነዉ።



# ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ መንስዔ እና የሚተላለፍበት መንገዶች

ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ መንስዔ በእሳተ ገሞራ አማካኝነት በተፈጠረና በሃሩራማ አካባቢዎች በሚገኝ የቀይ ሸክላ አፈር ላይ ለረዥም ጊዜ በባዶ እግር በመሄድ ነው ። ተላላፊ ያልሆነዉ ዝሆኔ ብዙ ጊዜ ተላለፊ ከሆነዉ የዝሆኔ በሽታ ጋር ይምታታል ። ነገር ግን ተላላፊ ያልሆነዉን ዝሆኔ የሚያመጣ ምንም አይነት ቫይረስ ፣ ባክቴሪያ ፣ ፈንገስ ወይም ጥገኛ ተህዋስ የለም ።

## ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ በሽታ ምልክቶች ምንድናቸው?

- የመጀመሪያ ደረጃ ምልክቶች አብዛኛውን ጊዜ የእግርን የላይኛው ቆዳን ማሳከክ እና የታችኛውን እግርና መርገጫዎችን የማቃጠል ስሜት ያካትታል
- በእግር የላይኛው ቆዳ ላይ የተሰራጨ ወፋፍራም እብጠቶች መፈጠር
- ከተሰነጠቀ ቆዳ የሚወጣ ፈሳሽ መኖር
- ወደኋላ ቆይቶ የሚፈጠሩት ጠጣር እብጠቶች ሁለት አይነት ሊሆኑ ይችላሉ ፣ ለስላሳ እና በፈሳሽ የተሞሉ ወይም ጠጣር እና በስሮች የተያያዙ ፤ አብዛኛውን ጊዜ ከጠጣር የቆዳ እብጠቶች ጋር የተያያዙ ናቸው
- አንዳንድ ጊዜ ህመምተኛው ትኩሳት ሊኖረው እንዲሁም እግሮቹን ሊያስነክሰውና ሊያመው ይችላል ።



## ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ በሽታ ህክምና እና መከላከያ መንገዶች

- ለህመም በሚያጋልጠው አፈር ላይ ሸፍን ጫማ ተጫምቶ መራመድ ወይም ቀጥተኛ ንክኪን መቀነስ
- በየቀኑ በንፁህ ውሃና በሳሙና እግርን መታጠብ
- በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ መሬቱን የሚሸፍን ምንጣፍ ወይም መሰል ነገር ማንጠፍ

## ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ ህክምና የሚከተሉትን ያጠቃልላል

- የእግር ንፅህናን ለመጠበቅ በንፁህ ውሃና በሳሙና መታጠብ (በሽታው በጀመረ ሰሞን ቢቻል በበረኪና መታጠብ ጠቃሚ ነው)
- የቆዳ እንክብካቤ ማድረግ - መደበኛ ፈሳሽ ቅባት ወይም ዘይት መጠቀም
- በየቀኑ ካልሲ እና ሸፍን ጫማ ማድረግ
- የሚለጠጥ ፋሻ መጠቀም
- እግርን ቀጥ አድርጎ መስቀል እና ማንቀሳቀስ
- በሠለጠኑ ባለሙያዎች እብጠቶቹን ለማስወገድ ቀላል ቀዶ ጥገና ማድረግ